ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

| | |
|---|---|
| **የተዛመዱ ርእሶች:-** | ACF, ACF-RA, COB-RA, IJA-RA, IOH-RA, IRB-RA, JHC, JHF, JHF-RA, JOA-RA |
| **ሃላፊ ፅ/ቤት:-** | የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ<br>የአካዴሚ ዋና መኮነን<br>ዋና የሥራ መኮነን |

# የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነትን ማስታወቅና መመርመር

## I. አላማ

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነትን ማስታወቅና መመርመር ቅደም ተከተሎችና መመርያዎች ለማስቀመጥ

## II. ፍቺዎች

A. *ማጎሳቆል ማለት*

1. የአንድ ልጅ ወይም ደካማ ኣዋቂ ማንኛውም፣ ሊታይ ወይም ላይታይ የሚችል አካላዊ ጉዳት፣ ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ልጁን ወይም ደካማ አዋቂውን የመንከባከብ ጊዚያዊ ወይም ዘላቂ ጠባቂነት ወይም ሃላፊነት ባለው በማንኛውም ግለሰብ፣[1] የልጁ ወይም የደካማው ኣዋቂ ጤና ወይም ደህንነት በመጎዳት ላይ ወይም የመጎዳት የተጨበጠ አደጋ ላይ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ መፈፀም።

2. ልጅን ወይም ደካማ ኣዋቂን የመንከባከብ ዘላቂ ወይም ጊዚያዊ ጠባቂነት ወይም ሃላፊነት ባለው በማንኛውም ግለሰብ በልጅ ወይም በደካማ ኣዋቂ ላይ የተፈፀመ ማንኛውም የፆታ ተግባር ወይም ተግባሮች (ኣካላዊ ጉዳቶች ይድረሱም ኣይድረሱም)፣ የፆታ ኣደጋ ወይም ብዝበዛ የሚያካትት፣ የዘመድ የፆታ ግንኙነት፣ መዳፈር፣ ወይም በማንኛውም ደረጃ የፆታ ጥቃት፣ ግብረ ሶዶም ወይም ከተፈጥሮ ውጭ የፆታ ልምዶችን የሚጨምር ነገር ግን በነዚህ ያልተወሰነ። ፆታዊ ኣመፅ ወይም መጠቃት የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን፣ ኣላግባብ መጋለጥ፣ የፆታ ብልት/ተግባር የማየት ጉጉት፣ መሳም፣ በእጅ መዳሰስ፣ ፆታዊ መቀራረቦች፣ በማንኛውም ደረጃ የሚፈፀም የፆታ ወንጀል፣ ኣስገድዶ መድፈር፣ ግብረ ሶዶም፣ ሽርሙጥና፣ በሰው መነገድ፣ ወይም የግብረሰጋ ግንኙነት ትርእይት፣ ፎቶግራፍ፣ ፊልም ማንሳት መፍቀድ፣ ማበረታታት፣ ወይም መሳተፍ፣ ወይም ልጅን ወይም ደካማ ኣዋቂን ከህግ ውጭ ኣድርጎ ማሳየት፣ ወይም ኣንድን ልጅ ወይም ኣንድን ደካማ ኣዋቂ ከለየለት/የተመዘገበ ፆታዊ ኣጥቂ ኣብሮ እንዲኖር ወይም በደምበኛነት ኣካባቢው እንዲገኝ መፍቀድ።

B. ልጅ ማለት ማንኛው(ዋ)ም የMontgomery County Public Schools (MCPS) ተማሪ፣ የልጁ/ጂቱ እድሜ የፈለገውን ይሁን፣ እና ሌላ እድሜው/ዋ ከ18 ኣመት በታች የሆነ/ች ግለሰብ ነው/ናት። የሚሪላንድ ህግ ባጠቃላይ እድሜው/ዋ ከ18 በላይ የሆነ/ች ተማሪ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ባይ(ት)ወነጀልም፣ MCPS የዚህ ኣይንቱ ስነምግባር ከዚህ በታች በተቀመጡት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ዘገባ እዲደረግ ይጠብቃል።

---

[1] ቋሚ ወይም ጊዝያዊ ጥበቃ ወይም ልጅን ወይም ደካማ ኣዋቂን የመንከባከብ ሃላፊነት ያለው ግለሰብ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ቤተሰብ ወይም ከቤተሰብ ጋር ኣብሮ የሚኖር፣ ጎረቤት፣ የMCPS ሰራተኛ፣ በጎ-ፈቃደኛ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ በስልጣን ላይ የሚገኝ ግለሰብ፣ ወይም ሌላ ግለሰብን ያካትታል።

C. *County Multi-Disciplinary Team/የካውንቲ ባለበርካታ-መስክ ድርጅቶች ቡድን (MDT*) እንደአግባቡ እየተገናኘ ምክርና የተቀነባበረ የህክምና ፕላን ዝግጅት የሚያደርግ የMontgomery County ወኪል ድርጅቶች የባለሙያዎች ቡድን ነው። የካውንቲ MDT የMontgomery County Tree House Child Assessment Cente/የትሪ ሃውስ የልጅ ግምገማ ማእከል እና የሚከተሉት የMontgomery County ወኪል ድርጅቶች ተወካዮችን ያካትታል፡-

1. The Montgomery County State's Attorney's Office/የስቴት ኣቃቤ ህግ ፅ/ቤት

2. The Special Victims Investigative Division of the Montgomery County Police Department/የፖሊስ መምርያ (MCPD) የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል

3. Child Welfare Services in the Montgomery County Department of Health and Human Services/በጤናና ሰብኣዊ ኣገልግሎቶች የልጅ ደህንነት ኣገልግሎቶች፣ በኣብዛኛው Child Protective Service/የልጅ ደህንነት ኣገልግሎት (CPS) ተብሎ የሚታወቀው፣ ወይም Aging and Disabilities Services Information and Assistance Unit in the Montgomery County Department of Health and Human Services/በጤናና ሰብኣዊ እገልግሎቶች ውስጥ የእርጅናና የስንክልናዎች ኣገልግሎቶች መረጃና እርዳታ ክፍል፣ በኣብዛኛው Adult Protective Services/ኣዋቂ ጥበቃ/መከላከያ ኣገልግሎቶች (APS) ተብሎ የሚታወቀው፣ በደካማ ኣዋቂዎች ጉዳይ።

የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት የተባሉ ጉዳዮች ተከሳሹ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የሆነበት፣ የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ/Contact፣ ወይም ተወካዩ፣ መወሰድ ያለበትን ተገቢ እርምጃ ለመወሰን፣ እንዲሁም በክውነውቶች ለመወያየት እና የተገኙ ትምህርቶችን እና የቀጣይ መሻሻል እድሎችን ለመገምገም የካውንቲ MDT ስብሰባዎች ለመከታተል ሊጋበዙ ይችላሉ።

በተጨማሪ፣ በት/ቤት-የተመደበ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን/Liaison ወይም ሌላ የMCPS ሰራተኛ የዘገባ ርእስ ለሆነ(ች)ው ተማሪ የተቀነባበረ ኣገልግሎቶች ለማቅረብ ኣላማ ብቻ የካውንቲ MDT ስብሰባ ሊ(ልት)ጋበዝ ይችላል/ትችላለች። መረጃዎች፣ ዘገባዎች፣ እና በካውንቲ MDT ኣማካይነት የተጋሩ ዘገባዎች በሁሉም ተሳታፊዎች በጥብቅ በሚስጢራዊነት መያዝ ኣለባቸው እናም በሜሪላንድ ህግ መሰረት ሳይፈቀድ እንዳይጋለጡ መጠበቅ ኣለባቸው።

D. *ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ ኣባል ማለት*፣ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በተባለው ወቅት፣ በልጁ ወይም ደካማ ኣዋቂ መኖርያ ቤት ኣብሮ የሚኖር፣ ወይም ዘወትር የሚገኝ ግለሰብ ማለት ነው። በመኖርያ ቤት መደበኛ ህላዌ ማለት የኣንድ ልጅ፣ ወይም የደካማ ኣዋቂ፣ ወይም የቤተሰብ ህይወት ትርጉም ያዘለ ኣካል የሚያደርገው ብቃት ካለው ብዛት ጋር የመኖርያ ቤት ጉብኝት ወይም ቆይታ ማለት ነው።

E. *የኣእምሮ ጉዳት* ሊታይ፣ ሊለይ የሚችል፣ እና የልጅ ወይም የደካማ ኣዋቂ ኣእምሮኣዊ ወይም ሳይኮሎጂካዊ የመስራት ችሎታ ከፍተኛ ብልሽት።

F. *የMCPS ሰራተኞች* የተመሰከረላቸውና ያልተመሰረከላቸው፣ ተተኪ መምህራንን ጨምሮ፣ በMCPS የተቀጠሩ ፐርሶኔል ናቸው።

G. *የMCPS ንብረት* ማለት ማንኛውም ት/ቤት ወይም ሌላ መገልገያ፣ የMCPS ንብረት የሆኑ ወይም በMCPS የሚካሄዱ ቦታዎች ጨምሮ፣ ኣውቶቡሶችና ሌሎች የMCPS ተሽከርካሪዎች፣ እናም የመስክ ጉዞዎችን ጨምሮ፣ ማናቸውም በMCPS ስፖንሰር የሚደረግ መገልገያና ቦታዎች ማለት ነው።

H. *የMCPS ስራ ተቋራጮች* ለMCPS ኣገልግሎቶች የሚሰጡ የውጭ ስራ ተቋራጮች እና ሌሎች ግለሰቦች ናቸው፣ የስራ ተቋራጩን ቀጥታ ሰራተኞች፣ የበታች ተቋራጮች፣ እና/ወይም ስራ ተቋራጩ ከMCPS ጋር ያለው ውል የሚጠይቀውን ስራ እንዲያከናውኑለት የሚጠቀምባቸውን ነፃ ስራ ተቋራጮች ጨምሮ። በዚህ ደንብ የተቀመጡት የተወሰኑ ከስራ ተቋራጭ-ጋር-የተያያዙ ሂደቶች በMCPS ስራ ተቋራጮች ተግባራዊነታቸው ለMCPS ኣገልግሎቶች በሚሰጡበት ግዜ ነው እናም ማናቸውንም ህጋዊ ግዴታዎች

ኣይወስኑም ወይም ኣይቀይሩም።

I. *የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ ማጎሳቆል መገናኛ* – የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ በት/ቤት ኣስተዳደር ፅ/ቤት የእሽታ ክፍል የስርኣት-ኣቀፍ የልጅ ማጎሳቆል መገናኛ ይሰይማል፣ ይህም ከካውንቲ MDT ጋር ምክክር ሲደረግ እና የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ማስታወቂያ ምላሽ የMCPS ሰራተኞች ለማስተባበር ለMCPS ተቀዳሚ ስርኣት-ኣቀፍ መገናኛ ይሆናል። በዚህ ደንብ የተለዩ ሃላፊነቶች ለማሟላት እንዲያግዙ የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ ማጎሳቆል መገናኛ ሌሎች የሰራተኛ ኣባላትን እንዳስፈላጊነቱ መሰየም ይችላል።

J. *የMCPS በጎ-ፈቃደኞች* በMCPS ደንብ IRB-RA፣ *በጎ-ፈቃደኞች በት/ቤቶች ውስጥ* በተቀመጡት ማሳሰቢያዎች መሰረት የMontgomery County ተማሪዎችን ለመደገፍ ጊዜኣቸውንና ሃይሎቻቸውን የሚሰጡ ወላጆች/ኣሳዳጊዎች እና ሌሎች የቤተሰብ ኣባሎችን፣ እንዲሁም በልጆች ትምህርት ፍላጎት ያላቸው የማህበረሰብ ኣባሎችን ያካትታል። በዚህ ደንብ የተቀመጡት የተወሰኑ ከበጎ-ፈቃድ-ጋር-የተያያዙ ሂደቶች በMCPS በጎ-ፈቃድ ተግባራዊነታቸው ለMCPS ኣገልግሎቶች በሚሰጡበት ግዜ ነው እናም ማናቸውንም ህጋዊ ግዴታዎች ኣይወስኑም ወይም ኣይቀይሩም።

K. *ቸልተኝነት* ማለት ኣንድን ልጅ ወይም ደካማ ኣዋቂ ብቻው(ዋ)ን መተው ማለት ነው[2] ወይም ሌላ ተገቢ እንክብካቤ ወይም ትኩረት የመስጠት ጉድለት ነው፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ እንክብካቤ ወይም ትኩረት መስጠት፣ በማናቸውም ወላጅ፣ ኣሳዳጊ፣ የቤተሰብ ወይም ኣብሮ ኗሪ ኣባል፣ ጎረቤት፣ የMCPS ሰራተኛ፣ በጎ-ፈቃደኛ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ በሃላፊነት ያለ/ች ግለሰብ፣ ወይም የሚከተሉትን በሚያመለክቱ ሁኔታዎች ስር በዘላቂነት ወይም በጊዜያዊነት እንክካቤ ወይም የማሳደግ ሃላፊነት ወይም ልጁ(ጂቱ)ን ወይም ደካማ ኣዋቂው(ዋ)ን የመቆጣጠር ሃላፊነት ያለው ሌላ ግለሰብ፦

1. የልጁ/ጂቱ ወይም የደካማ ኣዋቂ ጤንነት ወይም ደህንነት መጎዳት ላይ ወይም ለጉዳት ኣስጊ ሁኔታ ላይ መገኘቱ፣ ወይም

2. የኣእምሮ መጎዳት በልጁ/ጂቱ ወይም በደካማ ኣዋቂ ላይ ወይም የኣእምሮ ጉዳት በከፍተኛ ኣስጊ ሁኔታ ላይ።

L. *በት/ቤት-የተመሰረተ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንኖች* – እያንዳንዱ/ዷ ርእሰመምህር እንድ የት/ቤት ኣማካሪ ወይም የሰራተኛ ኣባል እንደ በት/ቤት-የተመሰረተ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን ብሎ ይመድባል/ትመድባለች። በት/ቤት-የተመሰረተ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን በት/ቤት-የተመሰረተ ፔርሶኔልን ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን በመለየት፣ በምዝገባም እና በመከላከል ሙያዊ ብልፅግና በመስጠት ርእሰመምህሩ(ሯ)ን ያግዛል/ታግዛለች። የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ዘገባ ከተደረገ በኋላ፣ በት/ቤት-የተመሰረተ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንኑ/ኗ ለክሱ ምላሽ በመስጠት እና ለካውንቲው MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ኣገናኝ እና ለተባለው ተማሪ ተጠቂ ድጋፍ ኣስተባባሪ በመሆን ርሰመምህሩ(ሯ)ን ይደግፋል/ትደግፋለች። በት/ቤት-የተመሰረተ ኣገናኝ መኮንኑ/ኗ የኣንድ ዘገባ ኣርእስት ለሆነ/ች ተማሪ የተባበረ ኣገልግሎቶች ለመስጠት ኣላማዎች ብቻ ወደ ካውንቲ MDT ስብሰባ ወይም መመካከር ሊ(ልት)ጋበዝ ይችላል/ትችላለች። በት/ቤት-የተመሰረተ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንኖች መጎሳቆልንና ቸልተኝነትን በመለየት፣ በማመልከት እና በመከላከል ኣላማ ያለው ሙያዊ ስልጠና ይቀበላሉ።

M. *ግብረመልስ* ማለት ኣንድን ግለሰብ በሚከተሉት ምክንያቶች የማስፈራራት ኣለዚያም የመቅጣት ተግባር ወይም ሂደት ነው—

1. ተጥሷል የተባለ ህግ፣ መመርያ፣ ወይም ደንብ ማመልከት፤ ወይም

2. ተጣሰ በተባለ ምርመራ መሳተፍ።

---

[2] በሜሪላንድ ውስጥ፣ ከ8 ኣመት በታች እድሜ የለው/ያላት ልጅ በመኖርያ ቤት፣ በት/ቤት፣ ወይም በመኪና ውስጥ፣ ቁጥጥር ከሚያ(ምታ)ደርግ እድሜው/ዋ ቢያንስ 13 ኣመት ከሆነ/ች የሚያ(ምታ)ስተማምን ግለሰብ ኣጃቢነት ጋር ካልሆነ በስተቀር ብቻው(ዋ)ን መተው እይቻልም።

N. *ደካማ ኣዋቂዎች* 18 ኣመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግላሰቦች በሚያ(ምታ)መለከተው ግለሰብ ለእለታዊ ፍላጎቶቻቸው ለመንካባከብ ኣካላዊ ወይም ኣእምሮኣዊ ችሎታ እነደሚሳናቸው የታመነባቸው ናቸው።

## III. ለMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ዘገባ የማቅረብ ሃላፊነት

A. ዘገባ የማቅረብ ሃላፊነት መጠን ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ማንኛውንም የተጠረጠረ የልጅ ወይም የደካማ ኣዋቂ መጎሳቆል ወይም ቸልታ ማመልከት/ዘገባ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡-

1. ተጠቂ የሚባለው/የምትባለው በግለሰብ ደረጃ በኣመልካቹ/ቿ ቢ(ብት)ታወቅም/ባ(ት)ይታወቅም።

2. ጥቃቱ ባለፈው ጊዜ መድረሱ ለማመን እስከተቻለ ድረስ፣ ምንም እንኳን ሁኔታው በተጋለጠ ወቅት ተጠቂው/ዋ ኣዋቂ ቢሆንም/ብትሆንም።

3. ልጁ/ልጂቱ ወይም ደካማው/ዋ ኣዋቂ የትም ይኑር/ትኑር እናም የተጠረጠረው መጎሳቆል ወይም ቸልታ ተፈፅመበት የተባለው የትም ቦታ ይሁን።

B. *የቃል ማመልከቻ/ዘገባ።* የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ስለተጠረጠረ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በኣፋጣኝ የቃል ዘገባ ማቅረብ ኣለባቸው።

1. **የCPS/APS ማስታወቂያ።** እያንዳንዱ መጎሳቆሉን ወይም ቸልታውን የጠረጠረ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የቃል ዘገባ/ማስታወቂያ መደረጉን ማረጋገጥ የግል ሃላፊነት ኣለበት።

   a) የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የቃል ማስታወቂያዎች ወድያውኑ፣ የ24-ሰኣት የቴሌፎን ኣገልግሎት (240-777-4417) ለሚይዘው፣ ለCPS መደረግ ኣለባቸው።

   b) የልጅ ማጎሳቆል ወይም የደካማ ኣዋቂ ቸልተኝነት ሁሉም ዘገባዎች በMontgomery County የጤናና የሰብኣዊ ኣገልግሎቶች መምርያ ውስጥ ለእርጅናና ስንክልናዎች መረጃና እርዳታ ክፍል (240-777-3000) መደረግ ኣለባቸው።

   c) ኣንድ ግለሰብ ማጎሳቆልን ወይም ቸልተኝነትን ስለ ማስታወቅ ጥርጣሬ ካለው/ካላት፣ ጥርጣሬውን ለCPS (ወይም APS ለደካማ ኣዋቂዎች) በማመልከት በኩል መሳሳት ኣለባቸው።

   d) የተጠረጠረን ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ከማቅረብ ኣስቀድሞ፣ የተጠረጠረውን ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ ትክክለኛነት ለመወሰን ምርመራ ማካሄድ የማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ ፈቃደኛ ሚና ኣይደለም።

   e) ኣንድ ልጅ ወይም ደካማ ኣዋቂ የተጠረጠረን ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በሚመለከት ለMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋረጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ መረጃ ቢያቀርብ/ብታቀርብ፣ ያ/ቺ ግለሰብ የተወሰኑ ተከታይ ጥያቄዎች ጉዳዩን እና ጉዳዮችን ኣጭር መግለጫ፣ የት እንደደረሱ፣ እና የተጠረተረው ኣጥቂ ስምና መግለጫ ሊ(ልት)ጠይቅ ይችላል/ትችላለች። ዘገባ ከመደረጉ በፊት፣ የሆነ ሆኖ፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ከተደጋገመ፣ ዝርዝር ቃለ-መጠይቅ ተፈላጊ ያልሆነ ኣሰቃቂ የኣእምሮ ሁኔታ እንዳያስከትል ከማንኛውም ተጠቂ ወይም ምስክር ከተባለ/ች ጥያቄና መልስ ወይም የፅሁፍ መግለጫ መጠየቅ የለባቸውም።

   f) ዘገባ ከመደረጉ በፊት፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ተጠርጣሪ ኣጥቂዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ ወይም ስለ ክውነቱ ከነሱ ጋር

መወያየት የለባቸውም።

g) ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ለመጠርጠር በቂ ምክንያት መኖሩን ለመወሰን የሚሞክሩ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የተጠረጠረ መጎሳቆልን ወይም ቸልተኝነትን እንዲከዱ ተማሪዎች ላይ ተፅእኖ ማድረግ የለባቸውም።

2. **የርእሰመምህር/የበላይ ተቆጣጣሪ ማስታወቂያ።** ለCPS (ወይም ለAPS ለደካማ አዋቂዎች) የቃል ዘገባ ከተደረገ በኋላ፣ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ፣ ዘጋቢው ግለሰብ ት/ቤት የሚ(ምት)ገኝ ከሆነ፣ ለርእሰመምህሩ/ሯ ወድያውኑ ማስታወቅ አለበ(ባ)ት። ዘገባ አቅራቢው/ዋ በት/ቤት-የተመሰረተ/ች ካልሆነ፣ ለሚሰሩበት የMCPS ፅ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪን፣ እንዲሁም ልጁ/ልጂቱ ወይም ደካማ አዋቂው/ዋ ለሚከታተለው ት/ቤት ርእሰመምህር፣ ያስታውቃል/ታስታውቃለች። CPS ወይም APS ኣመልካቹ(ቿ)ን ምርመራውን እየተወ(ች)ው ወይም እያጣራ(ች)ው መሆኑ(ኗ)ን ቢነግርም/ብትነግርም ማስታወቂያው የግድ መደረግ ኣለበት።

a) ማስታወቂያ እንደተደረገ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ ከዚህ በታች በክፍል IV እንደተቀመጠው ተከታይ ቅደም-ተከተሎችን ይጀምራል/ትጀምራለች፣ እናም እታች በክፍል III(B)(3)(c) በተቀመጡት ሁኔታዎች መሰረት የMCPDን የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍልን ይገናኛሉ።

b) ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ዘገባው ኣንዴ ከቀረበ በኋላ፣ በክፍል IV ከተቀመጠው በስተቀር ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ማንኛውም ሌሎች የMCPS ሰራተኞች ማንኛቸውንም የውስጥ ምርምራ ማካሄድ የለባቸውም።

c) ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ የቃል ዘገባ በክፍል III(B)(1) እላይ በተገለፀው መሰረት መደረጉን እና የፅሁፍ ዘገባ በክፍል III(C) ታች በተገለፀው መሰረት ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ ኣለባቸው።

d) ይህ ደንብ ለርእሰመምህር ወይም ተቆጣጣሪን ማስታወቅ የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ማስታወቂያው የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች፣ የዘገባ ግዴታዎች ኣያሟላም። እላይ እንደተገለፀው፣ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ማመልከትም በተጨማሪ ይፈለግባቸዋል።

e) የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የት/ቤት ርእሰመምህርን ወይም ቀጥተኛ የበላይ ተቆጣጣሪን ስለ ማሳወቅ ቅሬታ በሚኖርበት ወቅቶች፣ ዘገባ አቅራቢው/ዋ በምትኩ/ኳ የMCPSን ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ኣገናኝ መኮንንን ማሳወቅ ይቻላል።

3. **የMCPD ማስታወቂያ።** ዘገባዎችን መከታተል ለማቃለልና ለማስተካከል፣ MCPS እና የካውንቲ MDT ኣባሎች ከMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ለሚቀርቡ የቃል ዘገባዎች ተቀዳሚ የዘገባ ወኪል ድርጅቶች መሆን ያለባቸው CPS (ወይም APS የደካማ አዋቂዎች ጉዳይ ሲሆን) መሆን እንዳለባቸው ተስማምተዋል። በተጨማሪ፣ የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ስለተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸለተኝነት ይመከራል እና/ወይም ወድያውኑ እንዲያውቀው ይደረጋል፡-

a) CPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የሚያካትት የቃል ዘገባ ሲደርሰው፣ CPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር በቅርብ እንደሚማካከር የMCPS ግንዛቤ ነው።

b) በቁጥጥራቸው ስር ያለ ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ዘገባ

ማቅረቡ(ቧ)ን ከማረጋገጥ በተጨማሪ፣ የተጠረጠረ *ፆታዊ ጥቃት* በክፍል II(A)(2) እላይ ፍች እንደተሰጠው፣ ወይም አዋቂ ተጠቂን የሚያካትት የፆታ ጥቃት የተጠረጠረ ማጎሳቆል ማስታወቂያ ከተቀበሉ፣ ርእሰመምህራን እና ተቆጣጣሪዎች ወድያውኑ ለMCPD ውስጥ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍልን ያስታውቃሉ።

c) ለሌሎች የተጠረጠሩ ማጎስቆል ወይም ቸልተኝነት ምላሽ ለመስጠት፣ MCPS ከMCPD ውስጥ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል እና፣ በሁሉም አስቸኳይ ሁኔታዎች፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የህዝብ ደህንነት ማገናኛ ማእከል (911) ወይም 301-279-8000 መደወል አለባቸው። MCPD በጉዳዩ ይካተት አይካተት፣ የሆነ ሆኖ፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች እላይ እንደተገለፀው በግልና በቀጥታ አስቸኳይ ዘገባ ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የማመልከት ግዴታቸውን አሁንም ማሟላት አለባቸው።

C. *የፅሁፍ ዘገባ።* የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት የቃል ዘገባ የሚ(ምታ)ደርገው ግለሰብ በMCPS ፎርም 335-44፣ *የተጠረጠረ የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባ* ላይ ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የፅሁፍ ዘገባ ገቢ ማድረግ አለበ(ባ)ት።

1. የፅሁፍ ዘገባው ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የተጠረረ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት መኖሩ አገናኙ ካጋለጠው በኋላ በ48 ሰአት ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት ምንም እንኳን CPS፣ APS፣ እና/ወይም MCPD ምርመራውን መቀፀል የተወው ወይም ፋይሉን እየዘጋው መሆኑን ለዘገባ አቅራቢው ያስታወቀ ቢሆንም፣ የፅሁፍ ዘገባው የግድ መደረግ አለበት።

2. የዘገባው ቅጂዎች በተራ ኤንቬሎፕ፣ ታሽገው፣ አድራሻ ሰፍሮባቸው፣ እና ሚስጢራዊ እሚል ምልክት ተደርጎባቸው ይሰራጫሉ። ኤንቬሎፑ በተለመደው የቢሮ-ለቢሮ ፖስታ መሸፈን አለባቸው። ቅጂዎች በMCPS ፎርም 335-44 ላይ እንደተመለከተው ለሚከተሉት መላካቸውን ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥታ ተቆጣጣሬ/ዋ ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች፦

   a) የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን፣ ቅጅዎችን በምስጢራዊ ማህደር የሚንከባከብ፤

   b) የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል፤ እና

   c) የMontgomery County ስቴት የአቃቤ ህግ ፅ/ቤት።

3. ርእሰመምህራን እና ተቆጣጣሪዎች ማናቸውንም የዘገባ ቅጂዎች አይይዙም፣ ነገር ግን የሚከተሉትን ብቻ የሚያካትቱ የሁሉንም የተዘገቡ ጉዳዮች ምስጢራዊ ማስታወሻ ደብተር ብቻ ይይዛሉ—

   a) የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ ስም፤

   b) የተጠረጠረ/ች በዳይ ስም፣ ከታወቀ/ች፤

   c) የቃል ዘገባው ቀንና ሰአት፤

   d) ዘገባው የተደረገ(ላ)ት የሰራተኛ አባል እና ወኪል ድርጅት ስም፤ እና

   e) ፎርሙ የተላከበት ቀን።

## IV. ጥርጣሬዎች ከተዘገቡ በኋላ ተከታታይ ሃላፊነቶች

A. ምርመራዎች

1. ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች እና ሌሎች የውጭ ወኪል ድርጅቶች ጋር በተጠረጠሩ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ምርመራዎች ሙሉ በሙሉ ይተባበራሉ። የነዚያን ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎች በሚመለከት መረጃ የመጋራት የጊዜ ቅደም ተከተሎች በMCPS እና በካውንቲው MDT አባሎች መካከል በተደረገው ስምምነት/Memorandum of Understanding ውስጥ ተቀምጠዋል። የካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎቻቸውን ወቅት እየጠበቁ እና የመማርያ ክፍልንና የት/ቤት ማህበረሰብ ረብሻን በመቀነስ ለማከናወን ተስማምተዋል።

2. በአንድ የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ምርመራ ወቅት CPS፣ APS፣ ወይም MCPD አንድን ተማሪ በMCPS ንብረት ላይ በትምህርት ሰአት ሊጠይቁ(ቋ)ት ይችላሉ። በሜሪላንድ ኮድ ደንቦች (COMAR) 13A.08.01.13 መሰረት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ አንድ የት/ቤት ባለስልጣን በቃለ-መጠይቁ ወቅት ይኑር አይኑር ይወስናል/ትወስናለች። ውሳኔ አወሳሰድ ላይ ርእሰመምህሩ/ሯ ከCPS፣ APS፣ ወይም ከMCPD ተወካዮች ጋር የመካከራል/ትመካከራለች። የት/ቤት ባለስልጣን መመረጥ አለበት፣ ከሚጠየቀው ተማሪ አስተያየት ተጨምሮበት፣ አንድ-በአንድ መሰረት ለተማሪው/ዋ ድጋፍና መፅናኛ ለመስጠት። የወላጆች/አሳዳጊዎች ማስታወቅ ሁኔታ እታች በክፍል IV.D. ይታያል።

3. የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በCPS፣ APS፣ MCPD፣ ወይም በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት ስለተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በእንጥልጥል ላይ የሚገኝ ምርመራ ላይ ተፅእኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛውንም እርምጃ መውሰድ የለባቸውም። ከመርማሪ ወኪል ድርጅቶች በቅድሚያ ፈቃድ ሳይገኝ MCPS በዳይ የተባለ(ች)ውን የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ መቅረቡን አይነግረውም/አይነግራትም።

B. የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በMCPS ንብረት ላይ እና/ወይም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞችን የሚያካትቱ ጥርጣሪዎች አያያዝ ተጨማሪ ቅደም-ተከተሎች

1. ክትትል በርእሰመምህር/ት ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ

   የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በMCPS ንብረት ላይ ወይም በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ተከናወነ የሚባል ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የሚያካትት የሚመለከት ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የተደረገ የቃል ዘገባ ማስታውቂያ ከተቀበሉ በኋላ ወዲያውኑ ርእሰመምህር ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳሉ፡-

   a) እላይ በክፍል III እንደተቀመጠው፣ የቃል ዘገባ ለCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) እንደተደረገ እና በ48 ሰአቶች ከዚያ በኋላ የፅሁፍ ዘገባ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ።

   b) እላይ በክፍል III እንደተቀመጠው፣ ፆታዊ ጥቃት የሚያካትቱ የተጠረጠሩ ክውነቶች ውስጥ የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍልን ማስታወቅ።

   c) Office of School Support and Improvement/የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ፅ/ቤት (OSSI)ን ተገናኙ እና ከMCPS ስርኣት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን ወይም ተወካዩ ጋር መመካከር።

   d) ከMCPS ስርኣት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን እና ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ከሚገኝ ተገቢ ድጋፍ ጋር፣ የተጠረጠረው አጥቂ ተጠቂ በተባለው እና በሌሎች ተማሪዎች ደህንነት ወድያውኑ አደጋ እንዳያስከትል ማረጋገጥ።

   e) ታች በክፍል IV(D) የተቀመጡትን እርምጃዎች በመከተል፣ ስለ ተማሪ ተጠቂዎች ለወላጆች/አሳዳጊዎች ፈጣን ማስታወቂያ ፕላን ለማዳበር፣ እንዲሁም ታች በክፍል IV(E) የተቀመጡትን እርምጃዎች በመከተል ሌሎችን በማህበረሰቡ ውስጥ ማሳወቅ

ማስፈለጉን ለመወሰን እናም ለዚህ ፕላን ለማዳበር፣ ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን እና ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጋር መተባበር።

2. ክትትል በMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን

የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በMCPS ንብረት ወይም በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ተከናወነ የሚባል ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ማስታወቂያ እንደ ተቀበለ፣ የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን፡-

a) ከCPS፣ MCPD እና ከሌሎች የካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጋር መገናኛ በእግባቡ መመስረቱን ያረጋግጣል።—

b) ኣጥቂ የተባለው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ የOffice of Employee Engagement and Labor Relations/የሰራተኛ ተሳትፎና የሰራተኛ ግንኙነት ፅ/ቤት (OEELR)ን ይገናኛል።

c) ለሁኔታው ምላሽ ለመስጠት ለርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ለቀጥተኛ ተቆጣጣሪ ቀጣይ ምክር እና ኣስፈላጊ ድጋፍ ለመስጠት፣ ከሌሎች የMCPS ሰራተኛ ኣባሎች ከOEELR፣ ከተማሪና ቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ፅ/ቤት፣ ከት/ቤት ደህንነትና ፅጥታ መምርያ የኣጠቃላይ ኣማከሪ ፅ/ቤት፣ እና ከመገናኛ ፅ/ቤት ጨምሮ ያስተባብራል።

3. ክትትል በOEELR

ኣጥቂ የተባለው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ፣ OEELR፡-

a) የባለጉዳይ ማህደር ይመሰርታል።

b) የተጠረጠረውን ኣጥቂ በሚመለከት ሌላ ተጨማሪ እንዳለ ለመወሰን የፔርሶኔል ማህደሮችና ይገመግማል።

c) ማንኛውም ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እስካለ ድረስ፣ ከርእሰመምህር/ተቆጣጣሪ፣ ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን፣ እና ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመመካከር፣ የተጠረጠረ(ች)ውን ኣጥቂ በኣስተዳደር ፈቃድ ወይም ኣለዚያ ተማሪዎች ጋ እንዳይ(ት)ደርስ፣ ፕላን ያዳብራል።

(1) OEELR የMCPSን ሰራተኛ የኣስተዳደር ፈቃድ ላይ ያደርገዋል፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር።

(2) ኣጥቂ ነው የተባለው የስራ ተቋራጭ ከሆነ፣ ኣቅራቢውን ለማሳወቅ እና በማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የተጠረጠረ(ች)ውን ግለሰብ ኣገልግሎቶቹን ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ለማቋረጥ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር፣ OEELR በOffice of the Chief Operating Officer/በዋናው የስራ መኮንን ፅ/ቤት (OCOO) ውስጥ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ኣብሮ ይሰራል/ትሰራለች።

(3) እጥቂ ነው የተባለ(ች)ው በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ፣ ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ግለሰቡ/ቧ በMCPS ንብረት ላይ ወይም MCPS ስፖንሰር ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በጎ-ፈቃድኛነቱ(ቷ)ን ለመገደብ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር፣ OEELR ከOSSI እና ከOCOO ኣብሮ ይሰራል/ትሰራለች።

(4) ይህን ፕላን በመተግበር ላይ፣ ኣጥቂ የተባለ(ች)ው ለኣስተዳደር ፈቃድ፣ የኣገልግሎቶች መቋረጥ፣ ወይም ለበጎፈቃድ ልዩ ጥቅሞች መታገድ ኣስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮች ብቻ እንዲያውቅ መደረጉን ለማረጋገጥ ጥንቃቄ መደረግ ኣለበት። የMCPS የሰራተኛ ኣባሎች፣ የምርመራው ሃቀኛነት ከመበከል ለመቆጠብ፣ ከመርማሪ ወኪል ድርጅቶች ፈቃድ በተቀዳሚ ሳይገኝ፣ በማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬዎች ከተጠርጣሪ ኣጥቂ ጋር ኣይወያዩም።

d) ተከታይ የMCPS ምርመራ። በእያንዳንዱ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የተጠረጠረ ማንሳቀል፣ ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ፣ OEELR ከሁሉም የMontgomery County የትምህርት (ቦርድ) መመርያዎችና የMCPS ደንቦች ጋር በተጣጣመ መንገድ የውስጥ ምርመራ ኣካሂዶ ተገቢ የዲሲፕሊን ሃሳብ ያቀርባል። ምንም እንኳን CPS፣ APS፣ እና MCPD ምንም እርምጃ ሳይወስዱ ጉዳዩን ኣጣርተው ቢለቁት ወይም ቢዘጉት እና/ወይም የስቴት ኣቃቤ ህግ የወንጀል ክስ መመስረት ባይቀበልም እንደዚህ ኣይነቶቹ ጉዳዮች የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ውሎች፣ እና/ወይም የሰራተኛ የስነምግባር ኮድን ጨምሮ ሌላ መመርያ መጣስ ሊያካትቱ ስለሚችሉ OEELR የውስጥ ምርመራውን ያካሂዳል።

(1) በCPS፣ APS፣ MCPD እና በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ፣ ከመርማሪ ወኪል ድርጀች በቅድሚያ ስምምነት ሳይገኝ፣ ወይምበነሱ የቀረቡ ማናቸውም ገደቦች ሁኔታ ሳይታይ፣ MCPS ከምስክሮች፣ ተጠቂ ከሚባሉ፣ ወይም የተጠረጠሩ በደለኞች ጋር ቃለ መጠይቅ ኣያካሄድም። በተጨማሪ፣ MCPS የውስጥ ምርመራዎችን ማካሄድ ያለበት ምርመራ በማካሄድ ላይ ከሚገኙት የውጭ ወኪል ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመተባበር መንፈስ እና የውጩ ምርመራ ላይ ጣልቃ የማይገባ ወይም ኣደጋ ላይ የማይጥል መሆን ኣለበት።

(2) ህግ እስከፈቀደ ድረስ፣ ተጠቂ የተባሉትንና የምስክሮችን ድግግሞች ቃለመጠይቅ ለማስቀረት፣ የMCPS ምርመራ በፖሊስ ዘገባዎች፣ ኣረፍተሃሳቦች፣ እና በ*በሜሪላንድ ኣኖቴትድ ኮድ Human Services Article, Section 1-202, to avoid repetitive questioning of alleged victims and witnesses መሰረት* ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ዘገባዎች ከተገኙ ሌሎች መረጃዎች መጠቀም ኣለበት።

(3) የMCPS ምርመራ ተቀዳሚ ኣላማ በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ እና በጎ-ፈቃደኛ የመጥፎ ስነምግባር መረጃ መኖር ኣለመኖሩን ለመወሰን ነው። በተጨማሪ፣ ምርመራው ጉዳዩ በህግ እና የቦርድ መመርያና የMCPS ደንቦች በሚጠይቁት መሰረት ዘገባው ቀርቦ እንደሆን፣ እና ተጨማሪ ሞያዊ እድገት እና ሌሎች የሂደት ብልፅግና ኣስፈልገው እንደሆነ መወሰን ኣለበት።

(4) ህጋዊ ሂደትንና የMCPS ሰራተኞች መብቶችን በሚመለከት፣ ምርመራው የቦርድ መመርያዎችን እና የMCPS ደንቦችን ማክበር ኣለበት፣ ለሰራተኛው(ዋ)ም ስለ ምርመራው ውጤቶች መነገር ኣለበት።

(5) የምርመራው ውጤቶች፣ ግለሰቡ/ቧ ለMCPS ኣገልግሎቶች እስከሰጠ ድረስ እና ለኣምስት ኣመቶች ከዚያም በኋላ፣ በOEELR ምስጢራዊ የምርመራ ማህደሮች ውስጥ ይያዛሉ። ከዚያም እነዚህ ማህደሮች በቋሚ መጋዘን ዉስጥ ይቀመጣሉ።

C. የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች

1. አንድ/ዷት በተጠረጠረ/ች ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት የተካተተ/ች ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ አስቸኳይ ህክምና ወይም የአእምሮ ጤንነት ህክምና ካስፈለገው/ጋት፣ ርእሰመምህርሩ/ሯ ወይም የርእሰምምህር ተወካይ ልጁ/ጂቱ ወድያውኑ ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ ሌላ መገልገያ ከተገቢ አዋቂ ቁጥጥር ጋር እንዲ(ድት)ወሰድ ያደርጋል/ታደርጋለች። የCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ተወካይ በቅድሚያ ወይም በተቻለ ወድያውኑ ከዚያ በኋላ እንዲያውቅ መደረግ አለበት። በሁሉም ሌሎች አስቸኳይ ላልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ MCPS ለልጁ/ጂቱ ወይም ደካማ አዋቂ ህክምና ወይም የአእምሮ ጤንነት ህክምናን በሚመለከት ከCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ተወካይ፣ ወይም ከMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር ይመካከራል።

2. በት/ቤት የሚገኘው የልጅ ማንሳቆል አገናኝ መኮንን የት/ቤት አማካሪዎች፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ ፒውፕል ፔርሶኔል ሰራተኞች፣ እና ሌሎች የMCPS ሰራተኞች፣ እንዲሁም የት/ቤት ነርሶች፣ የማንሳቆል ወይም የቸልተኝነት ጥርጣሬዎች ለማመልከት ወይም ለማረጋገጥ ወደፊት ለሚመጡ ተማሪዎች ድጋፍና ምክር ለመስጠት መገኘታቸውን ለማመቻቸት ያግዛል።

3. የማንሳቆል ወይም የቸልተኝነት ተጠቂ ለሆነ/ች፣ እንዲሁም ማንሳቆልና ቸልተኝነት ለሚያስታውቁ ተማሪዎች፣ አገልግሎቶች ለማቀነባበር፣ የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መንሳቆል አገናኝ መኮንን ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች፣ የMCPSን ፔርሶኔል እና ተማሪዎችን ምስጢራዊነት የሚጠብቁ እና ያልተፈቀደ የዘገባዎች መጋለጥ እና ማንስቆልና ቸልተኝነትን የሚመለከቱ ዘገባዎችን የሚከልክሉ ህጎች እስከፈቀዱ ድረስ ሊመካከር ይችላል። ሌሎች የMCPS የሰራተኛ አባሎች በካውንቲ MDT ስብሰባዎች ወይም ምክክሮች በMCPS እና በሌሎች የካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር በተመሰረቱ ቅደም-ተከተሎች መሰረት መሳተፍ ይችላሉ።

4. ኣንድ ርእሰመምህር ኣንድ የመንሳቆል ወይም የቸልተኝነት ምርመራ ኣርእስት የሆነ/ች ተማሪ ምርመራ ከተጀመረ በሶስት ወሮች ውስጥ ከኣካባቢ ት/ቤቱ/ቷ ራሱ(ሷ)ን ካገለለ/ች እና/ወይም ከወጣ/ች፣ ርእሰመምህሩ/ሯ የMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መንሳቆል ኣገናኝ መኮንንን ማስታወቅ ኣለበ(ባ)ት፣ እሱ(ሷም፣ በተራው/ዋ፣ ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር እንደ ኣግባቡ ይመካከራል/ትመካከራለች።

D. የተማሪ ተጠቂዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ማስታወቅ

1. ርእሰመምህራን፣ በተጠረጠረ መንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የተካተቱ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎችን ማን እንደሚያሳውቃቸው እና ያ ማስታወቂያ መቸ እንደሚሆን ለመወሰን ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መንሳቆል ኣገናኝ መኮንን እና ከCPS፣ APS (ለደካማ ኣዋቂዎች)፣ እና/ወይም ከMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር ይተባበራሉ። MCPS ተደረገ በሚባል ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የተካተቱ ተማሪዎች ወላጆ/አሳዳጊዎችን የማስታወቅ ሃላፊነት የለውም፡- (a) ኣጥቂ የተባለ(ች)ው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ያልሆነ(ች)በት፣ እና የተባለው ማንሳቆል በMCPS ንብረት ላይ ያልሆነበት ጉዳዮች፤ ወይም (b) በርእሰምምህሩ/ሯ እና በCPS፣ በAPS (ለደካማ ኣዋቂዎች)፣ እና በMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ግምት፣ ወላጆች/ኣሳዳጊዎችን ማስታወቅ ለተማሪው/ዋ ደህንነት ስጋት ሊፈጥር የሚችል (ለምሳሌ ኣንድ ወላጅ/ኣሳዳጊ ወይም የቤተሰብ ወይም የመኖርያ ቤት ኣባል ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ፈፅሟል ተብሎ የተጠየቀ) ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ምርመራን የሚያደናቅፉ ጉዳዮች። ማስታወቅ የMCPS ሃላፊነት ባልሆነባቸው ጉዳዮች፣ CPS፣ በAPS (ለደካማ ኣዋቂዎች)፣ ወይም የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ወላጆች/ኣሳዳጊዎችን ለማስታወቅ ሃላፊዎች ናቸው።

2. ከወላጆች/ኣሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ለማቃለል ከተፈለገ MCPS ምስጢራዊ የትርጉም ኣገለግሎቶች ያቀርባል።

3. ኣንድ ተማሪ ለጥያቄ ወይም ለህክምና ምርመራ ያለ ወላጅ ፈቃድ ከት/ቤት ቦታ ሊነሳ ኣይችልም

ከነዚህ ሁኔታዎች በስተቀር—

a) የMontgomery County የጤና እና የሰብኣዊ ኣገልግሎቶች መምርያ ልጁ(ጂቱ)ን ለማንሳት የጠባቂ ወይም የመጠለያ እንክብካቤ ስልጣን ካለው፤ ወይም

b) ተማሪው/ዋ አስቸኳይ ህክምና ካስፈለገው/ጋት።

4. ኣንድ/ዲት ተማሪ ሲ(ስት)ወገድ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ የመወገዱን ማስታወቂያ ለወላጆች/ኣሳዳጊዎች ወድያው መደረጉን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች። በጋራ ስምምነት፣ የዚህ ኣይነቱ ማስታወቂያ፣ ጉዳይ በጉዳይ መሰረት፣ ለCPS፣ APS (ለደካማ ኣዋቂዎች)፣ ወይም ለMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል መተላለፍ ይችላል።

E. ለሌሎች በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ማስታወቅ

1. ርእሰመምህሩ/ሯ በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ሌሎች ማስታወቂያ ይደረግላቸው እንደሆነ ለመወሰን እና ይህንኑ ለመፈፀም የጊዜ ፕሮግራም ጨምሮ፣ ፕላን ለማዳበር ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን፣ የMCPS የመገናኛ ፅ/ቤት፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር ይተባበራል/ትተባበራለች።

a) ማንኛውም ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ እና ከመታሰር ወይም ክስ ከመመስረቱ በፊት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን፣ የMCPS የመገናኛ ፅ/ቤት፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንደዚህ ኣይነት የት/ቤት ማህበረሰብ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ካላስከተለ በስተቀር በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ሌሎችን የማሳወቅ ተግባር ኣይኖርም—

(1) ተጠቂ ለተባለው የላቀ ጥቅም የሚያተርፍ ከሆነ፤

(2) በመካሄድ ላይ በሚገኝ ምርመራ ጣልቃ የማይገባ ከሆነ፤ ወይም

(3) በሜሪላንድ ህግ የተከለከለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የሚመለከት ያልተፈቀደ የመዛግብት ወይም ዘገባዎች መጋለጥ የማይጠይቅ ከሆነ።

b) MCPD፣ በተቻለ መጠን በቅድሚያ፣ MCPSን በጅምር ላይ ያለ እስራት ወይም የክስ ምስረታ የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ክውነት በMCPS ንብረት ላይ የተካሄደ ወይም የተጠረጠረው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የት እንደነበረ ለመንገር ተስማምቷል። ቁጥጥር ስር ማዋልን ከት/ቤት ንብረት ርቀው እና ከትምህርት ሰኣቶች ውጭ፣ በተቻለ መጠን እንዲደረጉ MCPS MCPDን ያበረታታል።

c) በMCPS ንብረት ላይ ተፈፀመ ተብሎ ለተጠረጠረ የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ክውነት እስራት መካሄዱን ወይም ክሶች መመስረታቸውን MCPS ሲደርስበት፣ ለማህበረሰቡ ተገቢ ማስታወቂያ ለማድረግ፣ እንዲሁም ለሌሎች ት/ቤቶች ማስታወቅ ተገቢ እንደሆነ ለመወሰን፣ ለምሳሌ፣ የታሰረው ግለሰብ ኣስቀድሞ ይሰራበት የነበረ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን፣ የMCPS የመገናኛ ፅ/ቤት፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር ይተባበራል/ትተባበራለች።

2. MCPS ማንኛውንም የማህበረሰብ ማስታወቂያ ለመተግበር የሚከተሉትን እንዲያንፀባርቁ ጥረት ያደርጋል—

a) በማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬ ተፅእኖ የተደረገባቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ብህትውነትና ምስጢራዊነት ይጠብቃል ወይም ማጎሳቆልን ወይም ቸልተኝነትን

የሚመለከቱ ያልተፈቀዱ መዛግብትና ዘገባዎች ከማጋለጥ ይቆጠባል፤

b) በካውንቲ MDT ውስጥ ያሉ ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጥርጣሬዎቹን በት/ቤት ማህበረሰብ የሚገኙትን የሁሉንም ተማሪዎች ደህንነት በሚያረጋግጥ መንገድ በሚገባ እየያዙት መሆናቸውን ለማህበረሰቡ ያረጋግጣል፤ እና

c) የተጠረጠረው ኣጥቂ ተገቢ ህጋዊ ሂደት እንደሚያገኝ እና *ከሜሪላንድ ህዝባዊ መረጃ ኣዋጅ ጋር የፀና ነው።*

3. የማህበረሰብ ማስታወቂያ ደብዳቤ፣ ኢሜይል ወይም ኤሌክትሮኒክ የቃል መልእክት ቅጂዎች ከMCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ኣገናኝ መኮንን ጋር ይጋራሉ።

4. በካውንቲ MDT የሚሳተፉ ወኪል ድርጅቶች፣ የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራዎቻቸውን በሚመለከት ከማህበረሰብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሻ በመስጠት የMCPS ሰራተኛ ኣባሎችን፣ እንደኣግባቡ፣ ለመደገፍ ተስማምተዋል።

## V. ምስጢራዊነት፣ መድህን፣ ከግብረመልስ መከላከል

A. በሜሪላድ ህግ፣ ማንም ሰው በቀና መንፈስ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኛነት ዘገባ የሚያከናውን ወይም በዘገባ የሚሳተፍ ወይም በምርመምራ ወይም በውጤቱ የህጋዊ ዳኝነት ሂደት የሚሳተፍ የማጎሳቆል ወይም ቸለተኛነት ዘገባ በማድረግ ወይም በምርመራ ወይም በህጋዊ ሂደት በመሳተፍ ሊደርስ ከሚችል የፍትሀብሄር ባለእዳነት ወይም የወንጀለኛ ቅጣት ነፃ ነው።

B. በሜሪላድ ህግ፣ ማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሆነ ብሎ በማጎሳቆልና ቸልተኛነት ዘገባ ማጨናገፍ ወይም ጠልቃ መግባት ኣይችልም። ይህን የሜሪላንድ ህግ የመጣስ ቅጣት ኣምስት ኣመት እስራት፣ የ$10,000 ቅጣት፣ ወይም ሁለቱም ነው።

C. የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

D. ተማሪዎች የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ተጠቂዎች ወይም ምስክሮች ሲሆኑ ወይም በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

E. በሜሪላንድ ህግ የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነትን የሚመለከት የመዛግብት ወይም የዘገባዎች ያልተፈቀደ መጋለጥ የወንጀለኝነት ጥቃት ነው። በተጨማሪ፣ ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ምንጩ እንዲገለፅ በህግ ካልተጠየቀ በስተቀር የዘጋቢውን ማንነት እንዲጠብቁ ይፈለግባቸዋል።

## VI. ሆን ብሎ/እያወቁ የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ኣለማቅረብ ወይም ዘገባ ሲደረግ ጣልቃ መግባት የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

A. ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፣ በሙያዊ ችሎታው ለMCPS በመስራት ላይ የሚገኝ፣ የልጅ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚጠረጥር እና እያወቀ ዘገባ ያላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ዘገባውን የሚከለክል ወይም ጣልቃ የሚገባ፣ እገዳ ወይም ስንብትን ጨምሮ፣ ዲሲፕሊን ይወሰድበታል።

B. ማንኛውም የMCPS ስራ ተቋራጭ፣ በኣገልግሎት ችሎታው ለMCPS በመስራት ላይ የሚገኝ፣ የልጅ ማንሳቀል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚጠረጥር እና እያወቀ ዘገባ ያላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ዘገባውን የሚከለክል ወይም ጣልቃ የሚገባ፣ ዲሲፕሊን ይወሰድበታል የኣገልግሎቶች መቋረጥን ጨምሮ።

C. ማንኛውም የMCPS በጎ-ፈቃደኛ፣ በበጎ-ፈቃድ ችሎታው ለMCPS በመስራት ላይ የሚገኝ፣ የልጅ ማንሳቀል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚጠረጥር እና እያወቀ ዘገባ ያላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ዘገባውን የሚከለክል ወይም ጣልቃ የሚገባ፣ ዲሲፕሊን ይወሰድበታል የበጎ-ፈቃድ ልዩ ጥቅሞች መቋረጥን ጨምሮ።

D. በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም በሌላ የስራ ፈቃድ ወይም የችሎታ የምስክር ወረቀት ሰጪ ቦርድ የተሰጠ ምስክርነት ሊታገድ ወይም ሊነሳ ይችላል፣ በሜሪላንድ ህግ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት፣ COMAR 13A.12.05.02ን ጨምሮ።

## VII. ከማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ጋር የተያያዙ ኣመፆች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

A. ኣንድ የMCPS ሰራተኛ በማንሳቀል ወይም በቸልተኝነት ተካትቷል/ተካታለች ወይም ኣለዝያ የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ወይም መመርያ፣ የMCPS ሰራተኛ የስነምግባር ኮድን ጨምሮ፣ ጥሷል/ጥሳለች ብሎ MCPS ከወሰነ ግለሰቡ/ቧ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል መታገድ ወይም ስንብትን ጨምሮ።

B. ኣንድ የMCPS የስራ ተቋራጭ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማንሳቀል ወይም በቸልተኝነት ተካትቷል/ተካታለች ወይም ኣለዝያ የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ወይም መመርያ፣ የMCPS ሰራተኛ የስነምግባር ኮድን ጨምሮ፣ ጥሷል/ጥሳለች ብሎ MCPS ከወሰነ ግለሰቡ/ቧ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል የኣገልግሎቶች ወይም የበጎ-ፈቃደኛ ልዩ ጥቅሞች መቋረጥ ጨምሮ፣ እንደኣግባቡ።

C. በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም በሌላ የስራ ፈቃድ ወይም የችሎታ የምስክር ወረቀት ሰጪ ቦርድ የተሰጠ ምስክርነት ሊታገድ ወይም ሊነሳ ይችላል፣ በሜሪላንድ ህግ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት፣ COMAR 13A.12.05.02ን ጨምሮ።

## VIII. የሙያ እድገት

A. MCPS፣ የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ ከሀገራዊና ከኣካባቢ ወኪል ድርጅቶች የባለሙያ ድጋፍ ጋር፣ የMCPS ሰራተኞች ይህን ደንብ በመተግበር ላይ ተገቢ ሞያዊ እድገት/ስልጠና ያቀርባል።

1. ከተማሪዎች ጋር መስራት ከመጀመራቸው በፊት፣ ሁሉም ኣዳዲስ የMCPS ሰራተኞች የልጅ ወይም የደካማ ኣዋቂ ማንሳቀልና ቸልተኝነት መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከል ኣስገዳጅ ስልጠና ይቀበላሉ። ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ይህን የኣዲስ ተቀጣሪ ስልጠና መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ OEELR ዘገባዎች ይይዛል።

2. በያንዳንዱ የትምህርት ኣመት መጀመርያ ላይ፣ ሁሉም ነባር የMCPS ሰራተኞች የልጅ ማንሳቀልና ቸልተኝነት መለየትና ዘገባ ዝግጅት ወቅታዊ እውቀትና ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ ኣስገዳጅ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ግምገማ የሚያካትት ስልጠና ይፈፅማሉ። ስልጠናዎች በድርጅቱ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች ፍላጎቶች እንደሚስማሙ ሆነው በተለይ ተስተካክለው በግምባር ወይም በመስመር ላይ ትምህርት በማካተት ይዘጋጃሉ። እንደ ኣግባቡ፣ ስልጠናው ለተጠርጣሪ ኣመፀኞች ህጋዊ ሂደትንም ይመለከታል። ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ኣስገዳጅ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ OEELR ዘገባዎች ይይዛል።

B. ከሃገራዊና ከኣካባቢ ባለሙያዎች፣ የካውንቲ MDT ሽሪክ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ፣ MCPS ወርክሾፖች፣ መረጃዎች፣ እና መስመር ላይ የስልጠና ሞድዩሎች፣ እንደ ኣግባቡ፣ ለMCPS በጎ-ፈቃደኞችን

ስራ ተቋራጮች፣ እንዲሁም ለወላጆችና ለሌሎች በሰፊው የMCPS ማህበረሰብ፣ ስለልጆችና ደካማ ኣዋቂዎች መጎሳቆልና ቸልተኝነት መለየት፣ ዘገባ፣ እና መከለከል፣ እንዲሁም እነዚህን የሚመለከት የቦርድ መመርያዎች እና የMCPS ደንቦች ያቀርባል።

C. በተጨማሪ፣ እነዚያ የMCPS በጎፈቃደኞችና ስራ ተቋራጮች ወደ ተማሪዎች መዳራሻ ያላቸውና የሚገናኙ፣ በMCPS ሰራተኞች በቀጥታ ቁጥጥር ስር ባልሆኑበት ሁኔታዎች፣ ስልጠና መቀበላቸውን እንዲመሰክሩ ይፈለግባቸዋል እና/ወይም መጎሳቆልና ቸልተኝነትን መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከል፣ ለMCPS ሰራተኞች ከተሰጠው ከሞያዊ እድገት ይዘት ጋር የሚጣጣሙ፣ እንደ ኣግባቡ፣መረጃያዊ ቁሳቁሶች ገምግመዋል። የምስክር ወረቀት ፎርሞቹን ቅጂዎች MCPS ይይዛል።

**የተዛመዱ ምንጮች** *Annotated Code of Maryland*: Education Article §6-113, Family Law Article, §§5-560, 5-561, 5-701, 5-702, 5-704, 5-705.2, 5-705, 5-706, 5-708, 14-303; Human Services Article, §1-202; *Code of Maryland Regulations* 07.02.07.04-.05, 07.02.07.19, 13A.12.05.02 and 13A.08.01.03

***የደንብ ታሪክ፡-*** ኣስቀድሞ የደንብ ቁ. 525-10፣ ዲሰምበር 17፣ 1980፣ እና የደንብ ቁ. 525-19፣ ዲሰምበር 30፣ 1980፤ ኦክቶበር 1983 የተከለሰ፤ ዲሰምበር 1986 የተከለሰ፤ ጃንዩወሪ 23 1989 የተከለሰ፤ ኦገስት 5፣ 2015 የተከለሰ፤ መለስተኛ ክለሳዎች ጁላይ 24፣ 2017።